ስማችን - - ኢወክንድ

ልሳናችን - - ነቅንቅ

ልዩ ዕትም ሰኔ 2002 ዓ.ም

## የኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ድርጅት (ኢወክንድ) አንደኛ ጉባዔውንና የምስረታ በዓሉን በተሳካ ሁኔታ አከናወነ

በሰኔ 22 ቀን 2001 ዓ.ም. በተደረገ የምስረታ በዓል የተወለደው ኢወክንድ የመጀመሪያውን ጉባዔ በካሊፎርኒያ ግዛት በሳንሆዜ ከተማ በሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በደመቀ ሁኔታ አካሂዷል።

ከተለያዩ ከሰሜን አሜሪካና ከካናዳ ከተሞች የመጡ ተወካይ አባሎች የተገኙበት ይህ አንደኛ ጉባዔ በተለያዩ አገራዊና ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊና ግልጽ ውይይት የተካሄደበት ከመሆኑም በላይ በዋና ዋና አገራዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቅ ግንዛቤ የተገኘበትና የወደፊቱን የትግል አቅጣጫያንና ስልት ያመላከት ጉባዔ ነበር ።

በዚህ የመጀመሪያ ጉባዔው ኢወክንድ ያለፈውን የአንድ አመት ጉዞ ዞር ብሎ የመረመረበትና የገመገመበት ከመሆኑም በላይ ለገጠሙ ችግሮችን ለተከሰቱ ድክመቶች ተገቢ መፍትሄ በመስጠት ጉባዔው እርምጃ የወሰደ ሲሆን ነባሩ የኢወክንድ አመራር በአጭር ጊዜ ውስጥ ያከናወናቸውን መልካም ተግባሮችና በኣንክሮ አጢኖ የድርጅቱ ጠንካራ ጎኖች በይበልጥ ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መመሪያ ሰጥቷል።

ማዕከሉን አገር ቤት በማድረግ ኢወክንድ በአጎራባች ሀገሮችና እንዲሁም በተለያዩ አህጉሮች ቅርንጫፎችን በማቋቋምና አካሎች በመመሥረት ድርጅታዊ አቋሙን በከፍተኛ ድረጃ ያጠናከረ ሲሆን ከቅርንጫፍ አካሎች ጋር የሚደረገው የሥራ ግንኙነትና ትስስር ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጉባዔው አዳዲስ የአሠራር ስልቶችን ቀይሷል። የሀገር ነቀርሳ የሆኖውን ወያኔን ለማስወገድ በሚደረገው ሁለ ገብ ትግል ሕዝባዊ ዓላማ ያላቸው ድርጅቶች የትግል ትብብር እንዲያደርጉ ጉባዔው ጥሪውን አስተላልፏል። በቀጣዩ የትግል ዘመን ለኢወክንድ የተቀላጠፈ አመራር ሊሰጡ የሚችሉ የአመራር አባላትን በመምረጥ ጉባዔው ተጠናቋል።

በጉባዔው ማግስት ሰኔ 24 ቀን በሳንሆዜ ከተማ የኢወክንድን የመጀመሪያ በዓል ለማክበር የደመቀ ሕዝባዊ ስብሰባ አካሂዷል። በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ በሳንሆዜ ከተማ ነዋሪ የሆኑና ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ በርካታ ኢትዮጵያውያንና እንዲሁም የኢሕአፓ አባላትና ደጋፊዎች የተገኙ ሲሆን፤ የኢሕአፓ ከፍተኛ አመራር አባላት ጓድ ኢያሱ አለማየሁና ጓድ ፋሲካ በለጠ፤ ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ እንዲሁም የዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ሊቀ መንበር ወ/ሮ ሙሉ ወርቅ አየለ ንግግር አድርገዋል። ስለ ኢወክንድ አመሠራረትና ዓላማ ገላጭ የሆነውና በሀገር ፍቅር የነደደው ጽሁፍ በወጣት ሳሚ የተነበበ ከመሆኑም በላይ በተደጋጋሚ የተደመጠው የወጣት ክንፈ ስነ ግጥም የቤቱን ስሜት በደስታና በፍቅር፣ በኩራት አሙቆታል። ከተለያዩ የወክንድ ቅርንጫፍ አካሎችና ከወክንድ ደጋፊዎች የተላኩ የደስታ መግለጫ መልእክቶችም ተነበዋል።

ኢወክንድ የቀደሙ የጀግኖች አያቶቹን ታሪክ ፈለግ ተከታይ መሆኑን ለመግልጽ በእለቱ በህመም ምክንያት በሥፍራው ባይገኙም ሁለት ታላላቅ አርበኞች - ኮሎነል አስናቀ እንግዳና ኮለኔል እምሩ ወንዴ - ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉት አስትዋጾ በወጣት ታዘብው አስፋ ወኔ የተሞላው ንግግር ቀርቦ የትግል የምስክር ወረቀት በበዓሉ ላይ ተበርክቶላቸዋል።

በመጨረሻም ከ40 አመት በላይ በትግል ውስጥ የቆዩት ጓድ ኢያሱ አለማየሁ ለወጣት ታዘበው አስፋ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማን ያስረከቡ ሲሆን ጓድ ፋሲካ በለጠ ደግሞ ለወጣት ሳሚ የኢሕአፓን አርማ አስርክበዋል። ለዘመናት የተባለው የኢሕአፓ የትግል መዝሙር ተዘምሮ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል።

Tel 202-291-5832 P.O.Box 56068 Washington DC 20040 e-mail: join@eprpy.com
www.eprpy.com